# አበበ ገላው ቤተ አማራን በሚመለከት ላቀረበው አቤቱታ የተሰጠ መልስ
ከ ኃይለ ኢየሱስ አዳሙ

ወንድም አበበ ገላው በግለሰብ ደረጃ በ ቤተ አማራ ልጆች ስድብ ደረሰብኝ፣ ፀረ አማራ የሚባል ውንጀላ ቀረበብኝ ብሎ አቤቱታ አቅርቡዋል ። እኔ እስከማውቀው ድረስ አንድም የቤተ አማራ ልጅ አበበ ገላውን በስም ጠቅሶ በግለሰብ ደረጃ የተሳደበ ወይም የወነጀለ የለም። የቤተ አማራ ልጆች በ አማራ ሕዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ከማሳወቅ በማህበራዊ እና ሌሎች መድረኮች ከመቀስቀስ ባለፈ ማንንም በግለሰብ ደረጃ ሲያብጠለጥሉ አልታዩም። ማንንም ሲሳደቡ አልሰማሁም አላየሁም። ወንድም አበበ ገላው ላቀረበው ስሞታ አንድም ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም። የቤተ አማራ ልጆች አበበ ገላውን በግል አልተሳደቡም። ሄኖክ የሺጥላ የተባለው ወንድማችን አበበ ገላውን በስም ጠቅሶ ሰሞኑን አንዳንድ የፃፋቸው ነገሮች ነበሩ። ሄኖክ ይሄን ነገር እንዲያቆም በግሌ ምክር ሰጥቸዋለሁ ። ይህ ማለት ሄኖክ የሺጥላ አበበ ገላውን የተቸበት ነጥብ ስህተት ሁኖ ሳይሆን አሁን እርስ በርሳችን እንተቻች ዘንድ ግዜ የማይሰጠ ከ ውጭ ድንበር እና ወንዝ ተሻግሮ የመጣ የ ትግራይ ነፃ አውጪ የሚባል ጠላት ስላለን ነው ። ሄኖክ የሺጥላ አሳማኝ የሆኑ በ አበበ ገላው ላይ የታዩ ያላቸውን አደርባይነቶች በማስረጃ አስደግፎ አቅርቡዋል።

ወንድም አበበ ገላው እሩዋጭ ፈይሳን ኦሮሞ ነው ብሎ መናገር ከቻለ የ ጎንደር ህዝብን ትግል የ አማራ ሕዝብ ትግል ብሎ ለመጥራት እንዴት ድፍረት አጣ የሚል ነው የ ሄኖክ ሙግት። ይሄ በርግጥ ጥሩ ሙግት ነው ። ስድብም አይመስለኝም። አንዳንድ የ ኦሮሞ ወንድሞች ሄኖክ ለማለት የፈለግው እንዴት አበበ ገላው እሩዋጭ ፈይሳን ኦሮሞ ነው ይላል ያለ መስሉዋቸው በ ወንድም ሄኖክ ላይ ብዙ የስድብ ናዳ ሲያወርዱ አይቻለሁ። ሄኖክ ለማለት የፈለገው ግን ለምን እሩዋጭ ፈይሳ ኦሮሞ ነው ተባለ ሳይሆን እንዴት አበበ ገላው እሩዋጭ ፈይሳን ኦሮሞ ነው ብሎ የ ጎንደርን ሕዝብ ትግል የ አማራ ሕዝብ ትግል ነው ለማለት አቅም አጣ ነው። በውስጥ መስመር ከሄኖክ ጋር በዚህ ጉዳይ ትንሽ ሙግት ውስጥ ገብተን ነበር ። ሙሉ የውይይታችንን ሃሳብ እዚህ ላይ ማቅረብ አልፈልግም። በዋናነት ግን እኔ ማወቅ የምፈልገው አበበ ገላው የ ጎንደር ሕዝብ ትግል የ አማራ ሕዝብ ለህልውናው የሚያደርገው ትግል ነው ብሎ አያምንም ወይ? ይሄንን ግልፅ አድርጎ ማስረዳት የ ወንድም አበበ ገላው ኃላፊነት ይመስለኛል። እኔ በግሌ ወንድም አበበ ገላው እንኩዋን የ አማራን ሕዝብ የህልውና ትግል ቀርቶ በመላው ዓለም ላይ የሰው ልጅ ለፍትህ፣ ለእኩልነት እና ለነፃነት የሚያደርገውን ሁሉ ትግል ይደግፋል ብዬ ነው የማምነው። በዓለም አደባባይ ያን የሞተውን ሰውዬ ሲያዋርድ የተናገረው ንግግር " "we need freedom" ነፃነትን እንፈልጋለን የሚል ነበር። እና እንዴት ነው የ ነፃነት መፈክርን ሳይፈራ በአንባገነኖች ፊት ያሰማ አበበ ገላው ዛሬ የ አማራ ሕዝብ ከ ትግራይ ወራሪዎች ነፃ ለመሆን የሚያደርገውን የ ነፃነት ትግል ይቃወማል የምንለው ?

በርግጥ አበበ ገላው በአስተዳዳሪነት የሚሰራበት ኢሳት በ አንዳንድ ዘገባዎቹ የ አማራ ሕዝብን ትግል የ አማራ ሕዝብ ትግል ብሎ በመዘገብ ፋንታ የ ጎንደር የ ጎጃም እያለ ለማቅረብ የሞከረበት ሁኔታ ተገቢ እንዳልነበር የ ቤተ አማራ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም የ አማራ ልጅ በ ወቅቱ ተናግሩዋል፣ አሳስቡዋል። ኢሳት መረጃዎችን ለሕዝብ በማድረስ ረገድ ትልቅ ኃላፊነት በመወጣት ላይ ያለ የ መገናኛ ተቁዋም ነው። ለዚህም ከፍ ያለ ምስጋና እና አክብሮት አለኝ ። ይህ ሲባል ግን መሻሻል ያለባቸው ነገሮች የሉም ማለት አይደለም ። በተለይም የ አማራን ሕዝብ ትግል የሚወክሉ ሰዎችን በማቅረብ የ አማራን ሕዝብ ትግል እና አላማ በትክክል መዘገብ ይኖርበታል ። በዚህ ረገድ በ እንግሊዘኛ የ ኢሳትን ዘገባዎች የሚፅፈው እንግዱ ወልዴ(Engidu Woldie) ግልፅ በሆነ መንገድ የአማራውን ትግል እየዘገበ ስለሆነ ምስጋናዬን ላቀርብለት እወዳለሁ። ሌላው ጉዳይ ወንድም አበበ ገላው አማራን ማዳን የሚቻለው ኢትዮጵያን በ ቅድሚያ ስናድን ነው የሚል አመለካከት እንዳለው ከሚሰጣቸው አስተያየቶች ለመረዳት ችያለሁ ። እዚህ ላይ ሁሉም ሊያውቀው የሚገባ ነገር ቢኖር የ አማራ ሕዝብ እያደረገ ያለው ትግል በ አማራ ማንነት እና በ አማራነት ላይ ያተኮረ መሆኑን ነው ። ወንድም አበበ ገላው ሊገነዘበው የሚገባው ጉዳይ በ አሁኑ ሰዓት የአማራ ሕዝብ በ ትግራይ ወራሪዎች ግልፅ የሆነ የ ጅምላ የዘር ማጥፋት ታውጆበት እራሱን ከፈፅሞ መጥፋት ለማዳን የሞት የሽረት ትግል ላይ ያለ ሕዝብ መሆኑን ነው ። አሁን ያለው ትግል አማራን ከፈፅሞ መጥፋት ለማዳን የሚደረግ ተጋድሎ ነው። ኢትዮጵያን የማዳን ኃላፊነት የሁሉም ድርሻ ነው። የ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የማስቀጠል ጉዳይ አማራ እራሱን ከተቃጣበት የፈፅሞ መጥፋት አደጋ ከተከላከለ በሁዋላ የሚታሰብበት ጉዳይ ነው። የ አማራ ሕዝብ ላለፉት 500 አመታት ኢትዮጵያን ለመገንባት ብሎ የራሱን ጥቅም አሳልፎ በመስጠት አሁን ላለበት ደረጃ ደርሱዋል። ታሪክ ለ አማራ ሕዝብ ሁለተኛ ዕድል አይሰጠውም። AMHARA Can't save Ethiopia while there's active genocide against poor AMHARA people all over Ethiopia!

***Haileeysus Adamu***